ምነዋ ኢሕአፓ ዴ (ኢሕአፓ አንድነት?)

በነሲቡ ስብሐት (አሉላ)

ኅዳር 01 ቀን 2008 ዓ.ም. (November 11, 2015)

ውድ ወገኖች! ስለ ያ ትውልድና ኢሕአፓ በሚፃፉ ጽሁፎች፣ በሚሰጡ ቃለ መጠይቆችም እና በመሳሰሉት ልክ አይደለም ያልኩትን ቀደም ሲል እንዳስነበብኩት ሁሉ ዛሬም ትዝብቴን ትጋሩኝ ዘንዳ ይህችን አጭር መልዕክት ላኩላችሁ። ስለ ኢሕአፓም ሆነ ስለ ያ ትውልድ የተዛባ ዘገባ አቅራቢዎች ዛሬ ዛሬ ከደርግና ከአጋሮቻቸው ባላነሰ ኢሕአፓ የነበሩና የሆኑም ናቸው። ይህ ጽሁፍ ዝርዝር አተታ ለማቅረብ ሳይሆን በዚህ ፀሐፊ አመለካከት የተናጋሪውን አባባል አድምጣችሁት በራሳችንም በኩል እንዴት እንደምንደበደብ ልብ እንድትሉት ነው።

በደርግ ቀይ ሽብር ዋና ፖሊሲ አውጪና የገዳዮች ቁንጮ ከነበሩት ሁለቱን የፋሽስቱን መንግሥቱ ኃ/ማርያምንና የረዳቱን ፍቅረስላሴ ወግደረስ መጽሐፍ ተከትሎ ሰሞኑን ደግሞ ያ ትውልድና ኢሕአፓ ላይ ሌላ ውንጀላውን ይዞ ብቅ ያለው የሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ መጽሐፍ ቀርቦልናል። "ከዝንጆሮ ቆንጆ ምን ይመራርጣል" እንዲሉ ከነዚህ በባህሪያቸው አንድ የሆኑ የዘመነ ደርግ ገዳዮች የምጠብቀው መጽሐፍ በመሆኑ አልተደነቅሁም።

ስለ ሌ/ኮሎኔል ፍሥሐ ደስታ "አብዮቱና ትዝታዬ" መጽሐፍ አስተያየቴን በቅርቡ በሰፊው እንደማስነብብ ቃል እየገባሁ የዚህ መልዕክቴ ዓላማው በቅርቡ የአቶ መርሻ ዮሴፍ ኢሕአፓ ዴ አመራር አባልና ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ ሰሎሞን ገ/ሥላሴ በ SBS ሬድዮ ለኮሎኔል ፍሥሐ ደስታ ያሻቦጎደጎዱትን ምስጋናና አድናቆት እንድታደምጡት ነው።

ኢሕአፓ እርጉዝ እንደገደለ፣ ኢሕአፓ አንድ ቤተሰብ እንደረሸነ፣ ኢሕአፓ የቦዘኔ ጥርቅም ነቱን የፃፉልንና አንድ ትውልድ ሳይሆን የገደልነው ከ2,200 አይበልጡም ብለው የሚያሾፉት የደርግ አባል "ወደፊትም እውነተኛው ፍርድ ይበየናል" በማለት ኢሕአፓንና በተአምር የተረፉትን አባላቱን ለፍርድ ለማቅረብ ደፍረው የጻፉት እኚህ የዘመነ ደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊ ኮለኔል ናቸው።

የኢሕአፓ ዴው ቃል አቀባይ አቶ ሰሎሞን ገ/ሥላሴ ደስታቸውንና ምስጋናቸውን እንዴት እንደሚገልጡላቸው አንሰማ። እናድምጥ።

(http://media.sbs.com.au/audio/amharic_151109_452087.mp3**) ለኢሕአፓና ለሀገር ብለው በየቀበሌው፣ ከፍተኛው፣ ወረዳ፣ አውራጃ፣ ክፍለ ሀገርና በየሜዳው በደርግ ገዳዮች በወደቁት ወገኖች ደም መቀለድ አይሆንምን?**

ኢሕአፓ ሲነሳ ቀይ ሽብር ይነሳልና የኮሎኔሉ መጽሐፍ አንኳሩ ስለ ቀይሽብር በማውሳት ኢሕአፓን ነብሰ ገዳይና የቦዘኔ ጥርቅም እያሉ ለዳግም ግድያ ሲያዘጋጁት ከኢሕአፓ ምላሻቸው ምስጋና ነውን? እውን ፀሐፊውስ "ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል" እንዲሉ የማንነታቸውን አስነብበዋል። ምነዋ የአቶ መርሻ ኢሕአፓ ዴ? ይህ ነው አቋማችሁ? አቶ ሰለሞን እንደ ቃል አቀባይነታቸው በግላቸው ሳይሆን ኢሕአፓ ዴን (የአሁኑን ኢሕአፓ አንድነትን) ወክለው ነውና ሙገሳቸው እኔስ ስለ ሁላችሁም አፈርሁ።

ምነዋ በዚህ ቃለ መጠይቅ ስለ ቀይ ሽብር አቶ ሰሎሞን ማንሳት ተሳናቸው? ስለ ሰውልጅ ፍትህና ግፍ በመጠኑም ቢሆን የሚያደምጡት የውጭ መንግስታት እንደ ቀልቤሳ ነገዎን፣ ከፊለኝ ዓለሙን ዓይነት ገዳዮች በአገኙት መረጃ ሀገራችን የወንጀለኞች ዋሻ አይደለችም በማለት ለፍርድ ሲያቀርቧቸው ዋና አዛዦቻቸውን ሚዛን የሚደፋ መጽሐፍ ብሎ ማሞገስ በቁም ያለነውንም ዳግም መግደል አይሆንምን?

በዘመነ ቀይ ሽብር ዋይታ ለማን ነበር? ሐዘንስ ለማን ነበር? ጩኸትስ? እየዬስ? ማን ያለ ጧሪ ቀረ? ማን ያለ አሳዳጊ ቀረ? ማን መመኪያውን አጣ? ማን ዕምቡጥ አበባውን ተቀጠፈ? ሀገር አይደለችንም እንዴ? በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ቤተሰብን ባዶ ያደረገ የደርግ ቀይ ሽብር እንዳይነሳ ፈላጊዎች ዛሬ ዛሬ ለማመን በሚከብድ መልኩ ያልተጠበቁት ናቸው። ትላንት የደርግ አጫፋሪ የነበሩትን ዛሬ መድረክ ሰጥቶ ለማስፏለል ቀይ ሽብር አይነሳም። በመቶዎች የሚቆጠር ደም በእጃቸው ያለ የደርግ ገዳዮች በየቦታው መታደን ሲጀምሩ ብቅ ያለውን የግምባራቸውን ሥር ለመሸፈን ትርጉም የሌለው "ብሔራዊ ዕርቅ" የሚያላዝኑ የማይጠበቁት ናቸው። "ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል" እንዲሉ ብሔራዊ ዕርቅ ሌላ፤ ወንጀለኛ ሌላ !!!

አሁን ጊዜው አመቺ ነው በማለት በያ ትውልድም ሆነ በኢሕአፓ ላይ የተያዘው ዘመቻ በደርግ አባ ወራዎች ብቻ ሳይሆን ኢሕአፓ ነን በሚሉትም መሆኑን ከታዘብኩ ከረምረም ብያለሁ። የኢሕአፓንና የያ ትውልድን እውነተኛ ታሪክ ሆን ተብሎ አቅጣጫ ለማሳት የሚፃፉ መጽሐፍትም ላይ ሆነ ሌላ ታሪኩን የሚያውቁ አግባብነት ያለው ምላሽ መስጠት፣ እየተወናበደና ግራ እየገባው ላለው ትውልድ ጠቀሜታውን በማጤን ማስረዳት ሲገባ እንኳን ደስ ያሎት ፈንጠዝያ ምን የሚሉት ይሆን?

እኔ ይህን ብያለሁ። መጽሐፉን ያነበባችሁ ካላችሁ የራሳችሁን ልትሉ ትችላላችሁ። ባታነቡትም ከአንድ የኢሕአፓ አመራር አይደለም ደጋፊ የዚህ ዓይነት ሙገሳ በሰማዕታት ዐጽም መቀለድ፣ በቋሚዎች ቁስል ላይ ደግሞ እንጨት ሳይሆን ጨዉ መስደድ ነው።

በዚህ ጉዳይና በመርዘኛው የኮሎኔሉ መጽሐፍ ያለኝን አስተያየት በቅርቡ ለማስነበብ ቃል እየገባሁ ለዛሬው የአቶ ሰለሞን ገ/ሥላሴን ሙግስና ቀጥሎ ያለውን Link በመጫን ያድምጡ።

http://media.sbs.com.au/audio/amharic_151109_452087.mp3

This is EPRP D?